# የቅንጅትን መንፈስ ያነቃቃ ሕዝባዊ ስብሰባ በካልጋሪ

በሜይ 7 ቀን 2006 በካልጋሪ፣ ካናዳ በቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ አዘጋጅነት በተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ አቶ አባተ ካሣ ከኒዮርክ፣ አርቲስት ታማኝ በየነ ከቨርጂኒያ ተገኝተው ለስድስት ሰዓታት የዘለቀ ደማቅና ስኬታማ የሆነ ሕዝባዊ ስብሰባ መካሄዱ ተገለጸ።

ስብሰባው የተጀመረው በወያኔ ጥይት በግፍ የወደቁትን ወገኖቻችንን ለአንድ ደቂቃ በህሊና ጸሎት በማሰብ ነበር።

ከዚያም መድረኩን ለአቶ አባተ ካሣ በማስረከብ "መንገዱ ቅንጅት ነው" በሚል ትምህርታዊ ሴሚናር ተጀመረ። ይህ ሴሚናር የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግር የዳሰሰና መፍትሔውንም ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ድንቅ ክንውን ነበር።

አቶ አባተ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ለምን ቅንጅትን እንደመረጠ፣ በሕዝብ ይሁንታ ያገኘ መንግሥት ለሀገር እድገትና ልማት እንዲሁም ሰላም ያለውን ጠቀሜታ፣ በሀገራችን በተደጋጋሚ ወርቃማ የለውጥ እድሎች ለምን እንደተነጠቁ፣ ዛሬ ያለው የወያኔ የማፊያ ቡድን በምሳሌነት ጠቅሰው "The God Father" የተሰኘውን ፊልም በማስታወስ ያላቸውን የባሕሪ አንድነት በማሳየት፣ እንዲሁም በርካታ አንኳር ነጥቦችን በማካተት ድምቅና ገልጽ ትምሕርታዊ ማብራሪያ አቅርበዋል።

አቶ አባተ ካሣ "ትላንት አባቶቻችን ሀገራችንን ከቅኝ ገዢዎች ጠብቀው ለኛ በክብር አስተላልፈዋል። ዛሬ ደግሞ እኛ ለልጆቻችን የሰው ልጅ መብት የሚከበርበት ሀገር ማቆየት አለብን" ሲሉ ለተሰብሳቢው አሳስበዋል።

በማጠቃለያቸውም ወደ ካልጋሪ ከመምጣታቸው በፊት በተለያዩ 12 የአሜሪካና የካናዳ ከተሞች እንዳደረጉት ሁሉ የዛሬው የለውጥ እድል እንዳያመልጠን ከፈለግን ማንም ሳይሆን ተዓምር የሚፈይድልን እኛው እራሳችን ስንደራጅ እንደሆነ በመግለጽ በአዳራሹ ከነበረው ተሰብሳቢ መካከል በጣም በርከት ያለው የቅንጅት ደጋፊ አባል ሆኖ እንዲመዘገብ በማድረግ ተደናቂውን ሴሚናር አጠናቀዋል።

ከሳቸው በመቀጠል መድረኩን እንዲረከብ አርቲስት ታማኝ በየነን የጋበዘችው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ውስጥ በአንጋፋነቷ የምትታወቀው ጋዜጠኛ ወይዘሮ ብዙ ወንድማገኝሁ ስትሆን አርቲስት ታማኝን ኢትዮጵያዊ ስሜቱን በሚመስጥ ትውስታ አስደምጣ መድረኩን ስታስረክበው ታማኝ በየነ መናገር እስኪያቅተው እንባ እየተናነቀው ነበር መድረኩን የተረከበው።

አርቲስት ታማኝ የ10 ዓመት ሕጻን የሚገድል፣ ባል አስሮ ሚስት የሚገድል አረመኔ እያየን እንዴት እንቀበል እንዴትስ እሺ እንበል በማለት ዛሬ ህሊና ያለው፣ ሀገሩን የሚወድ፣

ቤተሰቡን የሚወድ፣ ኢትዮጵያዊ ለማንም ሳይሆን ለራሱ ህሊና ሲል ይህን እንቢ አልቀበልም እንዲል ከልብ በመነጨ ስሜት ይገልጽ ጀመር።

ታማኝ በመቀጠልም ስንቶቻችን ነን ዛሬ ለሕዝባችን ብለን ከማዕረጋችን፣ ከተድላ ኑሮአችን ወጥተን ከ300 መቶ እስረኛ ጋር ሲሚንቶ ላይ እየተኛን በአንድ ጉድጓድ ልንፀዳዳ የተዘጋጀን? ይህ ምን ማለት ነው? ወገናችን ለመብቱ የሚያደርገውን ትግል እያየን የሰላም እንቅልፍ ይወስደን ይሆን? አይመስለኝም ሲል ለተሰብሳቢው እየወረወረ መልሱም ዝም ማለት እንደማይገባ እያሳወቀ በመደራጀት ሕዝብ ያመነውን፣ የደገፈውን፣ የመረጠውን አካል በምንችለው ሁሉ በመደገፍ ትግሉን ዳር ማድረስ እንደሚገባን ስሜትን በሚቀሰቅስና በሚያነቃቃ ገለጻ አቅርቦታል። የእናቶችን ዋይታና እሪታ በማንሳትና በማስታወስም ለተሰብሳቢው የወያኔን አረመኔያዊ ተግባር ቁልጭ አድርጎ በማሳየት መልዕክቱን አጠናቂል።

ለስድስት ሰዓታት በንቃት ሳይሰላች የተቀመጠው ተሰብሳቢ በካልጋሪ የቅንጅት ድጋፍ አካል የተዘጋጀውን የቅንጅት አርማ የያዘ ቲሸርት በተወካዩ በአቶ ታዬ ሙሉጌታ አማካኝነት ለአቶ አባተ ካሣና ለአርቲስት ታማኝ በየነ ከተበረከተ በኋላ ሁለቱም ፊርማ ያኖሩበት አንድ ቲሸርት ደግሞ በታማኝ አማካኝነት ለጨረታ ቀርቦ በ3 ሺ አምስት መቶ የካናዳ ዶላር በጨረታ ተሸጧል።

ተሰበሳቢው ቀድሞ እንዳደረገው ሁሉ ከቅንጅት ጎን ቆሞ ድጋፉን ለመስጠትና ትግሉን በፅናት ለማካሄድ ቃል ኪዳኑን በማደስ ስብሰባው ተጠናቂል።

በመዝጊያውም አቶ ሚካኤል ንጉሤ የካልጋሪ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ አባል የግንቦት 97 ቱን ምርጫ በማስመልከት ማለትም የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ የወያኔን አገዛዝ በምርጫ ድል ያደረገበትን አንደኛ ዓመት መታሰቢያ በካልጋሪም ከተማ እንደሚከበር በማስታወቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከታች በተጠቀሰው ቀንና ቦታ እንዲገኝ ጥሪ አቅርበዋል።

**Date:** **Sunday, May 14 , 2006**

**Address:** **Old Y Community Hall** **(Ethiopian Community Hall)**
**101-223- 12th Avenue SE**

**Time:** **3:00 P.M.**

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

በካልጋሪ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ